# አራተኛ ትምህርት

*ከጥር 13 — 19* *Jan 21-27/2017*

## የመንፈስ ቅዱስ የግል ባህሪ

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 16:13-14፣ ሮሜ 8:14-16፣ ሮሜ 15:13፣ ዮሐ. 14:6፣ ዮሐ. 17:17፣ ሮሜ 5:5።

> **የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-“አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኳችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” (ዮሐ. 14:26)።**

መንፈስ ቅዱስ አልፎ አልፎም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ በነፋስ ወይም በእሳት መልክ በመገለጡ አንዳንዶች የራሱ የሆነ የግል ባህሪ ማለትም መለኮታዊ ኃይል እንደሌለው ሲቆጥሩ ይስተዋላል። በዚህም እርሱን እንደ አንድ ራሱን የቻለ--ሕያው መለኮታዊ አካል ከመቁጠር ይልቅ በኃይል እንደሚሞላን የኤልክትሪክ ሞገድ ወደ መመልከቱ ያዘነብላሉ። እዚህ ላይ ጥያቄው ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች--መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል የሌለው በሚመስል ተግባር ወይም ተጽእኖ ላይ ሆኖ የሚያመለክቱበት ሁኔታ የለም ወይ?-የሚል አይደለም። ይልቁንም--የእርሱን የግል ባህሪ በአዎንታዊ የሚገልጹልን አያሌ ጥቅሶች የሉም ወይ?--የሚለው የጥያቄው ዐውድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ማን እንደ ሆነ የላቀና የተሟላ ምስል ለማግኘት የሚያስችሉን ጥቅሶች አሉ። በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ትኩረት ማድረግ የእኛ ፋንታ ይሆናል።

በሳምንቱ ጥናታችን መሪ ጥቅስ እንደ ቀረበው በዚህ ሳምንት ስለ መንፈስ ቅዱስ የግል ባህሪ አብልጠን እንማራለን። ይህ እውነት የእግዚአብሔር መለኮታዊ መንፈስ በህይወታችን ስላለው ሚና በተሻለ እንድናስተውል ይረዳናል። መንፈስ ቅዱስ የግል ባህሪ እንዳለው ማመናችን ለመንፈሳዊ ህይወታችን ያለውን ፋይዳ በጥልቅ እንድናስተውል ይረዳናል። ስለ እርሱ ትክክለኛ የሆነውን አስተሳሰብ ብቻ በአእምሮአችን የምንይዝ ከሆነ--የእርሱ የሆነውን ፍቅር፣ አምልኮ፣ ውዳሴ፣ መተማመንና ፍጹም ታዛዥነት በማሳየት ለእርሱ አጸፋዊ ምላሽ የምንሰጥ እንሆናለን።

*እሁድ ጥር 14* *Jan 22*

### የሱስ መንፈስ ቅዱስን የገለጸበት መንገድ

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ዮሐ. 16:13-14፣ ዮሐ. 15:26-27፣ ዮሐ. 14:17፣ 26። የሱስ በጥቅሶቹ በተለይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የግል ባህሪ የገለጻቸው ነጥቦች ምንድ ናቸው? የሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደ ረዳት ወይም አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) መግለጡ ለእርስዎ ምን ዓይነት ትርጉም ይሰጦታል?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የሱስ እንደ ተናገረው መንፈስ ቅዱስ--ይመራናል፣ ይናገረናል፣ ይሰማናል፣ ይገልጽልናል፣ ያከብረዋል (ዮሐ. 16:13-14)። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ--ያስተምረናል፣ ያሳስበናል (ዮሐ. 14:26)። በእኛ ውስጥ ይኖራል (ዮሐ. 14:17)፣ ምስክር ይሆናል (ዮሐ. 15:24)፤ ይወቅሳል (16:8)። እነዚህ ሁሉ የራሱ የሆነ

የግል ባህሪ ያለው ዘላለማዊ ማንነትን ያንጸባርቃሉ እንጂ የዚህን ተቃራኒ ማንነት ዐልባ ኃይል አይገልጹም፡፡

የሱስ በዮሐ. 14:16-18 የሰጠው ተስፋ ፍጻሜ ያገኘው እንዴት ነበር? ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ያልተተዉት እንዴት ነበር?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የሱስ ለተከታዮቹ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፡፡ ደቀ መዛሙርቱን ወላጅ እንደ ሌላቸው ልጆች የትም እንደማይተዋቸው የተናገረው የሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ተስፋ ሰጥቶአቸዋል፡፡ የሱስ በተለይ በዚህ ቦታ "ሌላ አጽናኝ" እንደሚልክላቸው ሲናገር ይደመጣል፡፡ እዚህ ላይ የሱስ የጠቀሳቸው ቃላቶች በእጅጉ አስፈላጊና መሰረታዊ ናቸው፡፡ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክኛው "ሌላ" በሚል የቀረበው ቃል " allos " በሚል ይታወቃል፡፡ ቃሉ--የራሱ የግል ባህሪ ያለው፣ ነገር ግን በባህሪው ከእርሱ ጋር አንድ የሆነ ሌላ አጽናኝ እንደሚልክ ያመላክታል፡፡ በሌላ አነጋገር የሱስ የእርሱን ቦታ የሚወስድ፣ ሥራውን በእኛ ውስጥ መሥራቱን የሚቀጥል-እንደ ራሱ ያለ የእርሱ ተወካይ እንደሚልክ ተስፋ እንደ ሰጠ እንመለከታለን፡፡

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የእርዳታ ሰጪው ወይም የአጽናኙ ሥራ ነው፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በዮሐ. 14:16 ለተጠቀሰው አጽናኝ  የተሰኘ ቃል የግሪኩን ጰራቅሊጦስ በቀጥታ ጥቅም ላይ የሚያውሉ ሲሆን--ይኸውም ለእኛ እርዳታና እገዛ እንዲሰጥ የተጠራውን መንፈስ ቅዱስ ለመግለጽ ነው፡፡ የሱስ እንደ የሱስነቱ የግል ባህሪ እንደነበረው ሁሉ መንፈስ ቅዱስም የግል ባህሪ አለው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ግላዊ ባህሪያት አልፎ አልፎ ተጠቅሰው መመልከታችን ለዚህ ጽንሰ ሃሳብ ከበቂ በላይ ድጋፍ ይሆናል (ዮሐ. 14:26፣ 15:26፣ ሐዋ. 15:28፣ ሮሜ. 8:26፣ 1ቆሮ. 12:11፣ 1ጢሞቴ. 4:1)፡፡

*መንፈስ ቅዱስ እንደው--ኃይል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የግሉ ባህሪ ያለው አምላክ መሆኑን ማወቃችን አብልጦ የሚያጽናናን ለምንድን ነው?*

*ሰኞ ጥር 15* *Jan 23*

## የመንፈስ ቅዱስ ግላዊ ገጽታዎች: ክፍል 1

ከዚህ በመቀጠል የቀረቡትን ጥቅሶች ሲያነቡ መንፈስ ቅዱስ፤ የራሱ ባህሪ እንደሌለው ኃይል ወይስ መለኮታዊ ባህሪ እንዳለው ሆኖ ተስሎ አገኙት? እስቲ ራስዎን ይጠይቁ፡፡

ሮሜ. 8:14-16፣ 27፣ ሮሜ. 15:30፣ 1ቆሮ. 2:10፣ ሐዋ. 8:29፣ 10:19-20፣ 28:25፡፡

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የራሱ የሆነ ባህሪ የሌለው ኃይል ስለ እኛ መማለድ ይችላል? የራሱ ባህሪ የሌለው መንፈስ ወይም ኃይል የእግዚአብሔር የሆኑትን ነገሮች ለመግለጽ የሚያስችል ችሎታ ሊኖረው ይችላል? መንፈስ ቅዱስ ኃይል--ከሚለው በተቃራኒ የራሱ ባህሪ ካለው ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ የተጠቀሱት ሁሉ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

በመቀጠል በቀረቡት ጥቅሶች በመንፈስ ቅዱስ ግላዊ ባህሪያትነት የተጠቀሱት ነገሮች ምንድን ናቸው? ኤፌ. 4:30፣ ሐዋ. 5:3፣ 9፣ 1ቆሮ. 12:11፣ ሮሜ. 15:30።

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እውቀት (ማስተዋል)፣ ስሜትና ፈቃድ የእርሱ የተለዩ ጸባዮቹ ናቸው። ማዘን የሚችለው የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው ብቻ ነው። ሊዋሽና ሊታለል የሚችለውም በተመሳሳይ የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው ነው። እንዲሁም የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው ብቻ በራሱ ምርጫና ውሳኔ--እንደ ፈቀደ ይሰጣል። የግል ፈቃድ--ለማንኛውም የራሱ ባህሪ ላለው እጅግ መሰረታዊ መለያና ጸባይ ነው። ይህንን ባህሪ የተላበሰ ብቻ የማፍቀር ችሎታ አለው። እውነተኛ ፍቅር በማይጨበጥ ምናባዊ ማንነት ውስጥ መጸነስ አይችልም። ፍቅር ከግላዊው ባህሪ ስሜት ውስጥ ይመነጫል። እነዚህ በግላዊ ባህሪያትነት የሚታመኑ ነገሮች መንፈስ ቅዱስ በራሱ ዕውቀት እንዳለው፣ በራሱ የሚያስተውል መሆኑን፣ የራሱ ፈቃድ እንዳለው፣ በራሱ የሚወስን መሆኑን እንዲሁም የማፍቀር ችሎታውን አመላካቾች ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ጥላ ወይም የማያቋርጥ የፍሰት ሂደት ወይም ደግሞ የራሱ ባህሪ የሌለው ኃይል አይደለም። እግዚአብሔር ራሱ --የራሱ ባህሪ ያለው አምላክ እንደ መሆኑ፤ መንፈስ ቅዱስም በተመሳሳይ መንገድ ተጠቅሶአል።

*"መንፈስ ቅዱስ የራሱ የግል ባህሪ አለው። ይህ ባይሆን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ለመንፈሳችን መመስከር ባልቻለ ነበር። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህሪ አለው። ይህ ባይሆን በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ የተደበቀውን ምስጢር መግለጥ ባልቻለ ነበር።"*–Ellen G. White, Evangelism , p. 617.

*መንፈስ ቅዱስ የራሱ ባህሪ እንዳለው የሚገልጽን መጽሐፍ ቅዱሳዊው ገጽታ ከእርሱ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ ይኖረዋል? መንፈስ ቅዱስ ከራሱ ከእግዚአብሔር ባህሪ በተቃራኒ የራሱ የሆነ ባህሪ የሌለው ኃይል ብቻ ቢሆን ምን የተለየ ነገር ይኖራል?*

*ማክሰኞ* *ጥር 16* *Jan 24*

## የመንፈስ ቅዱስ ግላዊ ገጽታዎች: ክፍል 2

እግዚአብሔር አብን ብዙም ሳንቸገር በተጨባጭ በዐይነ ህሊናችን መሳል የምንችል ሲሆን--በተመሳሳይ ወደ መንፈስ ቅዱስ ስንመጣ ግን ይህን ባህሪ በቀላሉ ለማስተዋል ተግዳሮቶች መኖራቸው እሙን ነው። እንዲሁም የሱስ ጥሩ ሆኖ በወንጌል መገለጹን ተከትሎ ብዙዎች ስለ እርሱ ሥር የሰደደ ዕውቀት አላቸው። የእኛን ተፈጥሮ የወሰደው የሱስ ሰብዓዊውን ቅርጽ ይዞ በመካከላችን ኖረ።

*መንፈስ ቅዱስ የተገለጸበት የማይዳሰስ፣ ምናባዊ ባህሪ ከአብና ከወልድ አኳያ ሲነጻጸር በእርግጥም የተለየ ነው።*

ይህን ተከትሎ መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ ግላዊ ባህሪ የሌለው--ኃይል ብቻ ነው ወደሚል ድምዳሜ አንዳንዶች ሲደርሱ ይታያሉ። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው-እንዲህ ያለውን ጽንሰ ሃሳብ ከመንፈስ ቅዱስ ተፈጥሮ ጋር ለማስተያየት ስንሞክር ፍትሐዊ ሆኖ አናገኘውም። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ የራሱ ባህሪ የሌለው ኃይል ብቻ ነው ካልን፤ ትርጉም ሊሰጡ የማይችሉ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማግኘታችን አይቀሬ ይሆናል።

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት ጥቅሶች በጥንቃቄ ካነበቡ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ግላዊ ባህሪ የሌለው ኃይል ብቻ አድርገው በመሳል ሃሳቡን ለመረዳት ይሞክሩ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግላዊ ባህሪ ከሌለው በቀር ጥቅሶቹ ትርጉም ዐልባ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

ሮሜ. 5:13

---

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1ቆሮ. 2:4

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

መንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ወይም ግላዊ ባህሪ የሌለው ተጽእኖ አሳዳሪ ቢሆን ኖሮ ሐዋርያት "ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል" (ሐዋ. 15:28) ሲሉ የተናገሩት የማይመስል አባባል በሆነ ነበር፡፡ በዚህ ፋንታ አነጋገሩ እንደ አብ እና ወልድ ሁሉ ሌላ ግላዊ ባህሪ ያለው መለኮት መኖሩን ያመላክተናል፡፡

በተጨማሪ አማኞች "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" መጠመቃቸውን አስመልክቶ--የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የየራሳቸው የግል ባህሪ ካላቸውና ሶስተኛው ግን የራሱ የሆነ የግል ባህሪ ከሌለው--እንዴት በሶስቱም ስም ይጠመቃሉ? መንፈስ ቅዱስ ግላዊ ባህሪ ከሌለው በእርግጥ ይህ ትርጉም የለሽ ይሆናል፡፡ እነዚህ ሶስቱም የአንድ ማንነት--አንድ አካልና አምሳል መሆናቸውን ተከትሎ እኛ ሁላችን በእነዚህ በሶስቱ ስም እንጠመቃለን፡፡ ስለዚህ መንስ ቅዱስ እንደ አብ እና ወልድ በተመሳሳይ ደረጃ ተገልጦአል፡፡

ኤለን ጂ. ኋይት በዚህ ዙሪያ እንዲህ ትላለች "የየራሳቸው ግላዊ ባህሪ ያላቸው ሶስት ሰማያዊ ሕያዋን አሉ… አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ"–Ellen G. White, Evangelism , p. 615. በተጨማሪ ኤለን ኋይት--መንፈስ ቅዱስ የራሱ ባህሪ እንዳለው በግልጽ ትናገራለች፡፡

*ረቡዕ ጥር 17* *Jan 25*

## የእውነት መንፈስ

በዮሐ. 14:6 እና 17:17 እንደምናነበው የእውነት ትርጓሜ ምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እውነት የተሰኘው ቃል በዮሐንስ ወንጌል እጅግ ቁልፍ ሃሳብ እንደ ያዘ እንመለከታለን፡፡ ዛሬ እውነትን የምናስተውልበት መንገድ በአብዛኛው እንደው በደምሳሳው እንጂ ጥርት ያለ አይደለም--ንድፈ ሃሳባዊ እንጂ በተግባር የሚገለጥ ዓይነት አይደለም፡፡ የምዕራቡ ዓለም እውነትን የሚያስተውልበት መንገድ በግሪክ ፈላስፎች የተቃኘውን እሳቤ ነው፡፡ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ፤ በተለይም በዮሐንስ ወንጌል፤ እውነት በጣም ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ትርጉም ይዞአል--የሱስ እውነት ነው (ዮሐ. 14:6)፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ ሁሉ (ዮሐ. 17:17፣ መዝ. 119:142) አምላካዊው እውነት እጅግ ምጥቀት ባለው መንገድ በየሱስ ክርስቶስ የግል ባህሪ ተገልጾአል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገሩለት እግዚአብሔር ራሱን በየሱስ በመግለጹ እውነተኛው የእግዚአብሔር ማንነት እውቀት በየሱስ አማካይነት ተሰጥቶናል፡፡

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ዮሐ. 15፡26 እና 16፡13። *መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ እንደመሆኑ ተግባሩ ምንድን ነው?*

የእውነት መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራን በዮሐ. 16፡13 ተነግሮናል። መንፈስ ቅዱስ ይህን የሚያደርገው እኛን ወደ የሱስ ክርስቶስ በማመላከት ሲሆን፤ ይኸውም እርሱ የነገረንን እንዲሁም ያደረገልንን (ዮሐ. 15፡26) እንድናስታውስ በመርዳት ነው። መንፈስ ቅዱስ እኛን ወደ እውነት የሚመራው በእጅጉ ግላዊ በሆነ መንገድ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሱስን በማጉላትና ከፍ አድርጎ በማሳየት ከእርሱ ጋር ሕያውና ታማኝ ግንኙነት እንድንመሰርት ይመራናል። የሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር በተነጋገረ ጊዜ እግዚአብሔር በመንፈስና በእውነት (ዮሐ. 4፡24) ሊመለክ እንደሚገባ ነግሯት ነበር። እኛም መንፈስ ቅዱስ ይመራን ዘንድ ልመናችንን ስናቀርብ፤ እርሱ ደግሞ--መንገድ፣ እውነትና ሕይወት (ዮሐ. 14፡6) ወደ ሆነው ወደ የሱስ ይመራናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረበው እውነት እንደ ሰብዓዊው ፍልስፍና የተድበሰበሰ ወይም በማይተገበር ንድፈ ሃሳብ የተቀመጠ አይደለም። እውነት--"እግዚአብሔር የእውነት አምላክ" (ዘዳ. 16፡13፣ መዝ. 31፡5) ተብሎ ከሚጠራው ፈጣሪያችንና አዳኛችን ጋር ልንመሰርት የሚገባንን እጅግ ጥልቀት ያለው ግላዊና ታማኝ ግንኙነት በአንድ አጠቃልሎ ይዞአል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር አብ የተላከልን (ዮሐ. 15፡26) መንፈስ ቅዱስ በትክክል "የእውነት መንፈስ" (ዮሐ.14:17) ተብሎ መጠራቱ--የግል ባህሪ እንዳለው ብቻ ሳይሆን መለኮትነቱንም ጭምር አመላካች ነው።

*ለእውነት ያለን እሳቤ በአብዛኛው በስምምነት የቀረቡ ጽንሰ ሃሳባዊ አመክንዮዎች ላይ የተመረኮዘ ነው-- ልክ እንደ modus ponens ፡--ይኸውም--"A እውነት ከሆነ B እውነት ይሆናል። A እውነት ነው። ስለዚህ በተመሳሳይ B እውነት ነው። በዚህም A ማለት B ነው። እንደ እውነት የምናስተውላቸው አያሌ ነገሮች በስምምነት የቀረቡ ጽንሰ ሃሳባዊ አመክንዮዎች ለመሆናቸው ጥያቄ የለውም። ነገሩ እንዲህ ከሆነ የእውነትን ጽንሰ ሃሳብ --የራሱ ግላዊ ባህሪ እንዳለው መለኮት አድርገን ማስተዋል የምንችለው እንዴት ነው?*

*መልስዎን በሰንበት ትምህርት ጥናት ላይ ለማቅረብ ይሞክሩ።*

*ሐሙስ ጥር 18 Jan 26*

## በመንፈስ ቅዱስ ማንነት ላይ የጠራ እሳቤ ባይኖረንስ?

በመንፈስ ቅዱስ ግላዊ ባህሪ ዙሪያ የሚነሳው ጥያቄ በእጅጉ አስፈላጊና ግዙፍ ተግባራዊ አንደምታዎችን ያካተተ ነው። "እርሱ መለኮታዊ ባህሪ ያለው ከሆነና እኛ ግን የግል ባህሪ እንደ ሌለው ተጽእኖ አሳዳሪ ብቻ የምናስበው ከሆነ፤ ለመለኮታዊው ባህሪ መስጠት የሚገባንን፤ የእርሱ የሆነውን--ታላቅ አክብሮት፣ ውዳሴና ፍቅር እየነፈግን ስርቆት በመፈጸም ላይ እንገኛለን።"–LeRoy Edwin Froom, The Coming of the Comforter , p. 40.

*መንፈስ ቅዱስን እንደ ሰውር መለኮታዊ ኃይል ብቻ የምናስበው ከሆነ-የላቀ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊኖረኝ የሚችለው እንዴት ነው? የሚለው በአእምሮአችን የሚመላለስ ይሆናል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህሪ እንዳለው ስናስብ-መንፈስ ቅዱስ በ እ ኔ ው ስ ጥ አ ብ ል ጦ መ ሥ ራ ት የ ሚ ች ለ ው እ ን ዴ ት ነ ው ?* ብለን የምንጠይቅ እንሆናለን። ወሳኙ ነጥብ፡--*መንፈስ ቅዱስን የራስዎ ማድረግ ይፈልጋሉ ወይስ መንፈስ ቅዱስ የራሱ እንዲያደርጎት ይሻሉ?* የሚለው ይሆናል። *የመንፈስን አርአያነት ለመቀበል ዳተኝነት ይስተዋልቦታል ወይስ በደስታ እየታዘዙ ሊከተሉት ፈቃደኛ ነዎት* (ሮሜ 8:12 — 14፣ ገላ. 5:18—24)? *መንፈስ ቅዱስን እርስዎ ባወጧቸው እቅዶች መሰረት ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ*

ወይስ በእርሱ ላይ አጥብቀው እየታመኑ የሱስ ክርስቶስን እየመሰሉ ያድጉ ዘንድ በልቡ ያለውን እንዲተገብር ይፈቅዱለታል? "ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ… ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው" (1ቆሮ. 6:19) የሚለውን ይህን መልእክት ምን ያህል በተጨባጭ አስተውለውታል? በየዕለት አካሄዶና አኗኗርዎ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ፈቃደኛ ነዎት?

በእነዚህ በሁለት ጥቅሶች--ማለትም በሮሜ 5:5 እና በኤፌ. 2:18-19 የመንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ፍቅር ትስስር የፈጠሩበት መንገድ ምን ይመስላል? ይህ ለእርስዎ በግልም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የየራሳቸው ግላዊ ባህሪ ያላቸው ብቻ አንዱ ከሌላው ጋር ጥምረት ፈጥሮ ለመሥራት አስበውበት ምርጫ ማድረግ ይችላሉ። እኛ እያንዳንዳችንን በግልም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን በኅብረት ከሚመራንና ከሚለውጠን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን እንድንሠራ ግብዣ ቀርቦልናል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ከሶስቱ አንድ አምሳልና አንድ አካል እግዚአብሔር--የራሱ ባህሪ እንዳለው እንደ አንዱ ከማንቀበለው ይልቅ-እንደ ሌለ ብንቆጥረው፣ ለሚያቀርብልን ግብዣ ጆሮዎቻችንን ብንደፍንና ሕይወትን መቀየር በሚችለው የእርሱ ኃይል ላይ ልቦቻችንን ብናደነድን የተሻለ ይሆናል። የወደቅን እንደ መሆናችን፤ ኃጢአት ያበላሸንን ፍጡራን የሚለውጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገናል። ሆኖም በተቃራኒ ልናደርግ የምንችለው የመጨረሻ ነገር ሊኖር ቢችል በውስጣችን መነሳሳት መፍጠር በሚችለው መንፈስ ቅዱስ ላይ ዐይኖቻችንን መጨፈን ነው። ምንም ይሁን ምን--አብልጠን ራሳችንን ለእርሱ መስጠት ይጠበቅብናል። በእኛ ውስጥ በመሥራት እኛን ሊጠቀምብን የሚሻው መንፈስ ቅዱስ የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው መለኮት መሆኑን አምነን ስንቀበል እግዚአብሔር የክርስትና ተሞክሮአችን አማካይ ሆኖ ይሰየማል።

"መንፈስ ቅዱስ እኛን ይጠቀምንብናል እንጂ መንፈስ ቅዱስን ልንጠቀምበት አንችልም።"– The Desire of Ages, p. 672. ኤለን ኋይት ምን ለማለት የፈለገች ይመስሉታል? ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ እኛን የሚጠቀምብን እንዴት ነው? (ፊልጵ. 2:13)

*አርብ ጥር 19* *Jan 27*

## ተጨማሪ ሀሳብ

Read Ellen G. White,The Desire of Ages, pp. 669-672, where she speaks about the Holy Spirit. Also read Evangelism , pp. 613-617.

"ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ 'ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ' " (ማቴ. 28:18-20)። የሱስ አገልጋዮቹ የተጠሩበትንና የሚሠሩትን ሥራ በመስጠት ሕዝቦችን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ "ስም" እያጠመቁ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ሲያዝ--"ስም" የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ሳይሆን በነጠላ መቀመጡን ልብ ይሏል። የሱስ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ-በሶስቱ "ስሞች" ሳይሆን "ስም" (በግሪክ ኦኖማ ) አጥምቁ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል። ይህ--አንድ ሆኖ ነገር ግን ሶስት ተፈጥሮ ስላለው አምላካችን ማንነት ሊገልጽልን የሚችል ብርቱ ማሳያ ነው ("እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ

እግዚአብሔር ነው” [ዘዳ. 6:4])፡፡ በዚህ ሳምንት ጥናት ለመጥቀስ እንደ ተሞከረው በአብ እና በወልድ ግላዊ ባህሪያት ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች አለመኖራቸው በተጨባጭ እየታወቀ--ነገር ግን እነዚሁ ጥያቄዎች በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነሱት ለምንድን ነው? አፍቃሪ፣ የሚጠነቀቅልንና የሚያጽናናን የራሱ የእግዚአብሔር ህልዎት በእኛ ውስጥና በእኛ አማካይነት እንደሚሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ይህ ደግሞ ራሱ መንፈስ ቅዱስና ተለይቶ የተቀመጠው የእርሱ ተግባር ነው፡፡ ይህ ከእኛ ጋር አብሮ የሚኖር መንፈስ እንደ አብ እና እንደ ወልድ ሁሉ የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው መሆኑን ማወቃችን እንዴት ግሩም ነው? በእርግጥ መንፈስ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ ለማስተዋል አዳጋች ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ብርሃን ወይም ነፋስ ዓይነቶቹን መሰረታዊ ነገሮች ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ ማስተዋል የማንችል እኛ--ከእነርሱ እጅግ ምስጢራዊ ባህሪ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ተፈጥሮ እንዴት ሙሉ ለሙሉ ማስተዋል እንችላለን?

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

-  በረቡዕ ጥናት እውነት የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው--የሱስ ክርስቶስ ሆኖ ለቀረበው ጥያቄ የሰጡትን መልስ ያቅርቡ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? የሱስ እውነት የሆነበት ምክንያቱ ምንድን ነው? በስምምነት ከቀረቡት ጽንሰ ሃሳባዊ አመክንዮዎች ባሻገር እውነትን በዚህ መልኩ የምናስተውለው ለምንድን ነው?
-  ኤለን ጂ. ኋይት የሚከተለውን ጽፋለች፡ “እንደ እግዚአብሔር ሁሉ የራሱ ግላዊ ባህሪ ያለው መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን እየተመላለሰ መሆኑን አጥብቀን ልናጤን ይገባል”–Ellen G. White , E v a n g e li s m , p. 616. መልእክቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ህልዎትና ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይነግረናል?
-  በዚህ ሳምንት ጥናታችን የተመለከትናቸውን ስለ መንፈስ ቅዱስ የቀረቡ አንዳንድ ባህሪያትንና ጸባዮች መለስ ብለው ይመልከቱ፡፡ ይበልጥ የተጽናኑት በየትኞቹ ነው? ምክንያትዎን በጥናቱ ላይ ለማካፈል ይሞክሩ፡፡  የራሱ የሆነ የግል ባህሪ የሌለውን ነገር ወይም ኃይል በተሻለ ሊያዛምዱት የሚችሉት ከምን ጋር ነው? የመልስዎ አንደምታዎች ምን ይመስላሉ?